ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

Efdpu@aol.com www.Finote.org

በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ
በ ጥር 14 ቀን 2011 ዓም የተላለፈ ሐተታ

# የሜንጫውና የግፍ አገዛዝ በትግላችን ይወገድ

ከእንግዲህና ከዚህ በላይ መደናገርና መዘናጋት ሀገር አጥፊ እንደሚሆን ግልጽ ነው ። ሰው መስሎኝ ድንጋይ ቆነጠጥኩ ብሏል የሰለቸው ሰው ።ቢንገር ቢንገር የማይሰሙና ህሊናቸውናና ሰብ ዕናቸውን የሸጡት ደነዞች ጋር ጉንጭ አልፋው መቆም ያለበት ነው ። መልእክታችን ለሕዝብ እንጂ ለነሱ አይደለምና እነሱን ለታሪክና ለፍርድ መዝግበን ወደ ግዳጃችን ማተኮሩ የተሻለ ይሆናል ። ስለሆነ ተጨባጭ ሁኔታው ሀቁ ሲነገራቸው በትጋት ዘረኛ ጣኦት የሚጠርቡለትን አቅጣጫ ልናስቀይራቸው የሚቻል አይደለም ። የሆድም ጉዳይ ነው--ለሆዳም ሀገር ዕምብርቱ ነው እንደተባለው ። የስልጣን ፍርፋሪም ፍለጋ ጉዳይ ነው--የሚገርመው አንዳንዶቹን ለከንቱ ኮሚቴ ሹመት እንኳን ሳያበቋቸው ጥግ አስይዘዋቸዋል ። ጀሮአቸው ላይ ተኝተዋል፤መስሚያቸው በኩክ ሳይሆን በአጉል ተስፋና ጥቅም ፍለጋ ተደፍኗል ። ትንሽ ሰው ሁሌም ትንሽ ነው፤ባንዳም እንዲሁ ።

የታላቁን አድዋ ድል ዓመት በዓል ስንዘክር የዚህን ሀቅነት መገንዘባችን አይቀሬ ነው ። ብዙ ሺ ኢትዮጵያዋን ዘር ሳይለዩ በጽኑ ኢትዮጵያዊነት ለሀገራቸው ተሰውተው ወራሪውን የጣሊያን ጦር ድባቅ መትተው ታሪክ ሰርተዋል። አድዋ ቢወለድም እናት ሀገሬ ኤርትራ ጌታዬ ሻዕቢያ ያለው ሟቹ የወያኔ መሪ ግን የአድዋ ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ምኑ ነው ብሎ እንደዘቀጠም የምንረሳው አይደለም ።በቅርቡ የተከበረው የካቲት 12 የሰማዕት ቀንም ለኢትዮጵያ ምን ያህል ደም እንደፈሰሰላት በበቂ አስተማሪ ነው ። ማንም ወሮበላና ጠባብ በቀላሉ ሊያጠፋው የሚችል ኢትዮጵያዊነት የለም ። በደም እመስዋዕትነት የተገነባች ሀገር ናትና ኢትዮጵያ ። ሆኖም ለሰላሳ ዕመታት በላይ የግንጠላ ሀይሎች ወግተዋትና በአሜሪካ ድጋፍም በላያዋ ላይ ለ28 ዕመታት ሰፍረውባት ያደረሱት ጉዳት በቀላሉ የሚታይ አይደለም ።የወያኔ ኢሕ አዴግ አገዛዝ ጸረ ሕዝብ ጸረ ዴሞክራሲ መሆን ብቻ ሳይሆን ጸረ ኢትዮጵያ ሆኖ 27 ዕመት አይቶብናል ። ኢትዮጵያን ማፍረስ ግባችን ነው ያሉ ዘረኞች ፤ትግላችን ጸረ አማራ ነው ብለው በይፋ ያስቀመጡ ጠባቦች፤ ሁሉም በየራሱ ተገንጥሎ የራሱን ነጻ መንግስት ያቁም ያሉና በመርሃ ግብራቸው ያሰፈሩ ጉዶች በኢህ አዴግ ጭምብል ስር ተሰባስበው ኢትዮጵያን ምንኛ እንደጎዱና ምንኛ አንድነቷን እንደሸረሸሩ ሁላችንም የምናውቀው ነው ። የግንጠላ መርሃ ግብር አርቃቂዎች፤ የትግራይን ካርታ አስፍተው ስለ የቢጌምድርና ወሎን መሬት የነጠቁቱ፤ የኢሕ አዴግ ተለጣፊ ሹመኞች ዛሬ ራሳቸውን መንግሥት ብለው ተሰባስበውና በተለመደው የምርጫ ቡላታቸውም በረጅሙ ሊሰየሙብን አቆብቁበዋል ። ከወያኔ ሻዕቢያ ጋር ተባብረው ከአሶሳ እስከ በደኖ፤አረካ አርባጉጉን የወለዱት አውሬዎችም ዛሬ የአገዛዙ አካል ሆነው አንሰራርተዋል ። ዛሬ ግብግቡና ዋናው ቅራኔ በሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ (ኢትዮጵያ) ና በጸረ ኢትዮጵያ ዘረኛ ሀይሎች መሃል ያለው ቅራኔ ነው ። ወያኔ የሚለውን በኦሕ ዴድ/ኦዴፓ መተካትም ይቻላል ። ቅራኒያችን ከሹሞቹና ዘረኛ አገዛዛቸው ጋር ነው ።የሚታረቅም ቅራኔ አይደለምና ለወሳኙ ትግል በጋራ መነሳት-መቀጠል አስፈላጊ ሀገር አድን ስምሪት ነው ።

ህሊናና ልቦና አልባ ሆኑና የዛሬ በርካታ ምሁር ተብዬዎች ወጥመድ ሳይገቡ ሊሸጡ የቸኮሉ አሳዎች በመሆን ለባለነፍጦቹ በመነጠፍ የሕዝብና የሀገርን ፍዳ አባብሰውት ይገኛሉ ። ሹሞቹ ዙሪያ ጮቤ ለመርገጥ በሀገር ቤትም በባዕድ ያሳዩን ቅሌት

ምሳሌ ነው ። ሰውየው ማን ነው? ቲማችን ቡድናችን የሚሉትስ የነማን ነው? ምን ይዘት አለው? ትላንት እነማን ነበሩ ብለን ስንጠይቅ መልሱ ግልጽ ሆኖ ሳለ በሀሰት ፕሮፓጋንዳ ጎርፍ አጥለቅልቀውን ለፍየል ሕመም በሬ አራጅ አድርገውን ነበር ። አዲስ አበባን ፍንፍኔ ብሎ የኦሮሞን ሕዝብ ልዩ ጥቅም ልናስጠብቅባት ወሰንን፤ቻልን ያለው ሹሙና ጓደኛው ነበሩ ። የወያኔን የጎሳ ፌዴራሊዝም እንከላከላለን አናፈርስም ያለው ሹሙ ነው ። የጀግና ትውልድን ትግል በፊደል ልዩነት ጠብ ሊወስንና ሊያቀል የጣረው የዚያን ትውልድ ጨፍጫፊ ኮለኔል ከሓራሬ አግባብቶ ሊመልስብን የጣረው ራሱ ሹሙ ነው ። 27 ዓመታት የወያኔ ተለጣፊ ፤የደህንነት ተቋም አባል፤ ጠባብ ኦሮሞ ነኝ ሲል የነበረውን ያቀፉትና የደገፉት አድርባዮችና ቅጥረኞች በሀገራችን ላይ ያደረሱት ጉዳት ይህ ነው የሚባል አይደለም። ጸረ አማራ ወዘተ ሆነው የቆዩት ሹሙና ጓደኞቹ ነበሩ ።ይህን ሁሉ ታዲያ ጤዛ ሳይተን አሽቀንጥረው ጥለው ሹሞቹ የሌላቸውን ኢትዮጵያዊነት ሊያላብሱ የጣሩት ሁሉ በሀገራችን ላይ የከፋ ወንጀል ፈጽመዋል ። የችግራችን ዕምብርት የሆነውን የወያኔ ህግ ና አዋጆች አናፈርስም ያለን ሹሙ ነው ። የትግራይን መሬት አሁንም ያሳፋብን ወይም እንዲያሠፉ ፈቃጅ ራሱ ነው ። ከሱዳን ሲተቃቀፍ የቁራና መሬት ልቀቁ ሲል አልሰማንም ።የድሃ በኢት ሲያፈርስና ሲያፈናቅል ለኤሚሬትስ ግን ለገሀርን ለግሷል፤ ወያኔዎች በቪላቸው ይንደላቀቃሉ፤በለገጣፎና በሌሎች ቦታዎች ህዝብ መጤና ህገ ወጥ እየተባለ በኢቱ ይፈርሳል ። ይህን የከፋ ሀቅ እየተቀበልን ያለነው ትላንት ሳይሆን ዛሬ ነው ። ሹሞቹ የመጡት ለኢትዮጵያ ሳይሆን በኢትዮጵያ ላይ መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም ። ግብራቸው ምስክር ሆኦ ያጋልጣቸዋል ።ግላችን ተፋፍሞ ምቀተል ያልበት ለዚህ ነው ።እንደ ሰመእቶታችና እንደ የሀይቲ ሕዝብ ስልጣን ላይ ያሉት ይውረዱ እሚል አድናና ሰልፉን ሳናቋርጥና በሀገር አቀፍ ደረጃ አፋፍመን ልናስወግዳቸው ይገባል ።ከሹሞቹ አገዛዝ እየተጠቅሙ ያሉት ጠባቦችና ጸረ ኢትዮጵያዎች ጥቂቶች ናቸው እንደ ወያኔ ። ብዙሃኑ እኛ ነን--የኢትዮጵያ ሕዝብ ።ሀይልም በእጃችን ነው--አምርረን ስንነሳባቸው የቡከኖቹ መንጋ ራርውን ቆልፎ ይበታተናል ። ይህ የማንምንበትና እውን ልናደርገውም የምንታገልለት ሀቅ ነው ።

ሐኪሞች እስኪመካከሩ በሽተኛ ሞተ እንዳይመጣብን ያለው ህገር አድን መፍትሔ የወያኔ ኢሕአዴግን ስርዓት በትግል ጥሎ የሽግግርን ሂደት እውን በማድረግ ሕዝባኢ መንግሥትን ለመመስረት መቻል ነው ። አፍሪካኖች ኢተርቱ ወጣቶች ይቸኩላሉ ጎኢዳናውን ግን የሚያውቁት አዛውንቶቹ ናቸው ያሉት አግባብ አለው ።የነበረንን የዘመናት የትግል ተመክሮ፤አድዋን፤ጸረ ሙሶሊኒ ትግልን፤የካቲት 66ና ጸረ ወያኔ ትግሉን ሁሉ መመዘን ማጤን ተስኖን፤ለባዕድ ዕዝ ተጎንባሽ ሆነን፤ኢትዮጵያን የመሰለች ታሪካዊ ሀገር በጎጥ ልንቀይራት ልናስንሳት መነሳት ማለት ቅልጥ ያለ ጸረ ኢትዮጵያነት፤ከህደት፤ባንዳነት ነው ። ጠባብነትና መከፋፈል ምን ያህል ለወያኔ ጠቅሞት እንደቆየ የሚያስረዳን ፈላጊ አይደለንም ።ሕዝብ ደማችን አንድ ነው ብሎ በጋራ በመነሳቱ ወያኔን ቀደም ባልታየ ቀውስ ከቶ ወደ ውድቀት አምርቶት ነበር።ይህ የትላንት ተመክሮአች ነው፤አሁንም የስርየት ጎዳናችን መሆኑም አያጠራጥርም ። አንድነታችንን በመሰርሰርና እርስ በርስ በማናከስ ላይ ወያኔዎቹ (በቀጥታም ሆነ በኢሕአዴግ ስም) ያተኮሩት ኢትዮጵያዊነትን ለማደባየት ነው ። ቅማንት ከአማራ፤አሮሞ ከጊዴዎ፤ሶማሌ ከኦሮሞ፤ኦሮሞ ከአማራ ወኧተመጋደሉ ለዘረኞቹ አገዛዝ መቀጠል አስፈላጊ ነው ። ይህን በማመንም ነው ሹሞቹ ጽንፈኞችን ሰብበውና የክብር እንግዳ ብለው ያመጡብን ። የሻዕቢያ ቅጥረኞችን ድርጅት ብለው ያሰማሩብን ።ለዚህም ነው ለሻዕቢያና ለአረቦች ያጎበደዱት ። በሶማሊያም ቀውስ ውስጥ መዘፈቅ የቀጠሉት ።የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም አልተጠበቀም ብቻ ሳይሆን አስልፈው ሰጥተውታል ። ለሱዳን፤ለአመሪካ፤ለነ ሳውዲ ። የሕዝብን ትግል ውጤት የእኛ ብለውም ነጥቀዋል። በሀሰት ላይ የተመሰረተ ተክለ ሰውነት በማራገብም ላይ ናቸው ። ነገር ባዋቂ እንዲሉ ገና ሹሙ ለቦታው ሲታጭ የተጎነጎነውን ጸረ

ኢትዮጵያ ሴራ ኢጋልጠንም ነበር ።ሹሙን አሻሽጡ ተብለ በዋሽንግተን ተጠርተው እዝ የተሰጣቸው መኖራቸውን በመጥቀስ የማሻሻጡ ዘመቻ እንዳይጠልፈንም ለማስጠንቀ መሞከራችንም ይታወሳል ።በአሜሪካ ግፊት የርዋንዳው ካጋሜና የዩጋንዳው ሙሴቬኒ ለሹሙ እውቅና ፤ውዳሴና ሽልማት እንዲሰጡም ተደረገ ። የቀለለውን አሞሌ ውድ ሊያደርጉ ማለት ነው ። የአሜሪካ ቅጥረኛ ሆነው ሀገርን ያጋለጡና በአያሌው የጎዱ፤ስንቱን አዛውንት ጄኔራል ለሞት የዳረጉን ከውስጥ ሆነው መንግሥታችን ያሉትን ቦርቡረው ያስጠፉ ሁሉ ከሹሙ ጎን ዛሬ አማካሪ፤ሹመት ተቀባይ ወዘተ በሚል ከበውት ይገኛሉ ። ብርሌ ከነቃ እየሆነ መጣባቸው እንጂ የዘመናት ዕንቅልፍ ሊያስተኙን ነበር ዕቅዳቸው። በዚያውም ቅኝ ገዢዎች አፍሪካን እንደሰረቁት ሁሉ ኢትዮጵያን ሊሰርቁን ። በስንት ደም ህልዋናዋ የተጠበቀውን ኢትዮጵያን ሊያወድሙብን ። የጽንፈኞችን ገንጣይ ነፍሰ ገዳዮች መፈንጫ ሊያደርጉን ።ይህን እምቢኝ ብሎ በሁሉም ፈርጅና መስከ መታገል ሲያንሰን ነው።

ጾስት ቸቋኝ፡ያልናቸውን አገአዝ በጽናት ታግለን ሶስተኛውን ሆኖ አራተኛ በሉኝ የሚለንን መታገልን ልንፈርና ልንተው አያቻለንም ።ሕዝብ ወሳኝ ይሁን ካልን በኋላ የእናቴ ትንግርት አለና ልንገስባችሁ የሚለንን ግብዝ በጫንቃችን ልንሸከም ሆነ የጥበት ጫማውን ልንስም የሚጠበቅም ሊሆን አይችልም ። ዴሞክራሲ ስንል ባጅተን አምባገነነትን፤ መብታችን ይከበር ስንል ቆይተን መብት አልባ መሆንን፤ወያኔ ይወገድ ብለን ኢሕአዴግ ነኝ ያለንን መቀበል፤ሉዓላዊነት ስንል ቆይተን ለባዕድ ያደረና ሀገርን እያስበላ ላለ ቡድን መስገድን፤ በሽግግር ሂደት ሳይሆን ዘረነትን ባስቀጠሉ ሹሞች አገዛዝ ስር መውደቅን ልንቀበል አንችልም ።ኢትዮጵያዊነት ሳይሆን የደደቢቶቹ ዓይነት ክህደትና የነህያልስላሴ ጉግሳና የነአስረሱ አይነት ማፈሪያ ባንዳነት ነው ።

ንቧንማ ሆኜ ብገባ ከሀገርየእናቴን ጠባዮች በጠዘጠኩ ነበር ሲል ሀይሉ ገሞራው ገጥሞተመኝቶ ነበር ።ዛሬ ብዙዎቹ ወደ ሀገር የገቡት የኢትዮጵያን ጠላቶች ሊጠዘጥዙ ሳይሆን ከጠላቶቿ ጋር ተቃቅፈው ሊነድፏት ነው ። ይህ ባይጥምም መራራ ሀቅ ነውና የሀገራችን ሕዝብ፤ኢትዮጵያ ያለ ሁሉ በመተባበር ጀምሮት የነበርን ትግል መቀጠልና ማፋፋም። ኢትዮጵያ ስላሉ ወያኔ ን ያስጨነቁት የአስተማሪና የሠአተኘ ፣ማህበራት በየካቲት ይዞታቸው ይመስረቱ ። ሰርተኦ አደሩ ሕዝብ አድማ ይምታ፤ሙት ከተማዎች ይበራከቱ ።በወያኔ ኢሕ አዴግና ደጋፊዎቹ ሁሉ ላይ ማዕቀብና ማግለሉ ይጠናከር ።

ድል በጋራ ትግል !!

አድማና  አመጽ ይበራከቱ!!

ኢትዮጵያዊነታችንን ሊያዘናጉን እየሞከሩ ያሉትን ሁሉ አምርረን እንታገል !!

ውድቀት ለዘረኝነት፤ለባንዳዎችና ጠባቦች በሞላ !!